# Union of Tigreans in North America (UTNA)
## ማሕበር ተጋሩ ሰሜን ኣሜሪካ (ማተሰኣ)

UTNA
P.O.BOX 73736
Washington, DC 20056
UTNA67@verizon.net

Tel. (202) 265-8702
Fax. (202) 265-8703

04/06/2010

**በኢትዮጵያችን በህዝብ ንቁ ተሳትፎ በመገንባት ላይ ያለው ዴሞክራሲያዊ ስርዓት በፅንፈኞች ሴራ ከቶ አይጎነተልም!!**

**ከትግራይ ተወላጆች ማህበር በሰሜን አሜሪካ የተሰጠ መግለጫ**

የኢትዮጵያ ህዝብ ለዘመናት እየተፈራረቁ እላዩ ላይ ሲፈነጩበት የነበሩትን የለየላቸው ኢ-ፍትሃዊና ኢ-ዴሞክራሲያዊ ስርዓቶችን ከሰንኮፋቸው በመንቀል ደግመው ላይመለሱ ከትብያ ቀላቅሎ በምትካቸው ሁሉም ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች በእኩልነት፣ በመከባበርና በመፈቃቀድ መንፈስ የሚኖሩባትንና በጋራ ጥረታቸው የሚያንፅዋትን አዲሲቱን ኢትዮጵያን በዴሞክራሲያዊ መሰረት ላይ መገንባቱን ከተያያዘው እንሆ ሁለት ዓሰርት ዓመታትን ሊደፍን ነው፡፡

በአያሌ ሺሕ ዓመታት የሚቆጠረውን አሸብራቂ ታሪኩን ይበልጥ በሚያደምቁትና ዘመናዊነትን በሚያላብሱት ጥቂት የትግሉና የጥረቱ ፋይዳዎች እንሆ አሸተው የሚጨበጥና የሚዳሰስ ፍሬ እያስገኙለት ይገኛሉ፡፡

በመሆኑም ዛሬ ኢትዮጵያ ሃገራችን በአፍሪካ አህጉር በግንባር ቀደምትነት በፈጣን የለውጥ ሃዲድ ላይ እየረሸከረከረች ሁሉን አቀፍ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ዲፕሎማሲያዊ ድሎችን በማስመዝገብ ወደፊት በመገስገስ ላይ ነች፡፡

ኢኮኖሚያቸው በነዳጅ ሃብት ላይ ካልተገነባው ሃገሮች መካከል ደቡብ አፍሪካን ተከትላ ባለፉት ስድስት ዓመታት ከ10-12% የሚሰላ ኢኮኖሚያዊ እድገት ያስመዘገበች ብቸኛ አፍሪካዊት ሃገር ሆናለች፡፡

በአጭር ጊዜ ውስጥ ተመርቆ ስራ ላይ ይውላል ተብሎ የሚጠበቀው የጣና በለስ የኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫ ግድብን ጨምሮ የግልገል ጊቤ አንድ፣ የግልገል ጊቤ ሁለትና የተከዜ የሃይል ማመንጫ ግዙፍ ግድቦች ወደ ተግባር ተሸጋግረው የሃገሪቱን የሃይል ፍላጎት ደረጃ በደረጃ በማርካት ላይ ይገኛሉ፡፡ በአሁኑ ጊዜ ግንባታው በመሳለጥ ላይ ያለውና እስከ አሁን ከተሰሩት በእጅጉ የላቀው ግዙፉን የግልገል ግቤ ሶስት፣ ከዚያም በቅደም ተከተል የሚገነቡትን የግልገል ጊቤ አራትና አምስት የሃይል ማመንጫ ግድቦችንና በሌሎች

የሃገሪቱ ክፍሎች በሚገኘው የሃገሪቱ ተፋሰስ መልክዓ ምድር ስር በልማቱ አሸንዳና ቦይ ውስጥ የሚካተቱን የልማት አውታሮች ልደት እውን ሲሆን ሃገራችንን ወደ ላቀ የሃይል የውጭ አቅርቦት እንደሚያሸጋግራት ከውጥኑ መተንበይ ይቻላል፡፡ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የምስራቅ አፍሪካ የኢኮኖሚ ነብር በመባል ትሞካሽ የነበረችውን ኬንያን በጀግኖች ልጆቿ በረጅም ርቀት ሯጮች እንደቀደመቻት ሁሉ በኢኮኖሚው ዘርፍም በህዝቦቿ ጥረት የኬንያን ኢኮኖሚ በማለፍ በአሁኑ ጊዜ አጠቃላይ ዓመታዊ ገቢዋን ወደ ላቀ ደረጃ ከፍ በማድረግ የምስራቅ አፍሪካ ቀንድን ሃገሮች በኢኮኖሚ ቁንጮነት በመምራት በአሁኑ ወቅት $36 ቢልዮን ዶላር ዓመታዊ ሃብት በማስመዝገብ በታሪኳ ታይቶ የማይታወቀውንና በሃገሪቱ ብር ሲለካ ወደ ግማሽ ትሪሊዮን ብር የሚጠጋ ዓመታዊ ኢኮኖሚያዊ ሃብት ባለቤት ሆናለች፡፡

የዛሬ ኢትዮጵያችን የመንግስት አስተዳደርና ባለቤትነት እየቀጨጨ የግሉ ክፍል ኢኮኖሚ በእርሻው፣ በኢንዱስትሪውና በሌሎች መስኮች እጅግ እየሰፋ በመሄድ ላይ የምትገኝ ሃገር ሆናለች፡፡ ከስምንት ዓመታት በፊት በውጭ የግል ባለሃብቶች ይንቀሳቀሱ የነበሩት የኢኮኖሚ ፕሮጀክቶች በቁጥር ከሃያ ሰባት ያልበለጡበት ወቅት ተቀይሮ በ2002 ዓመት ላይ 4600 ልዩ ልዩ ፕሮጅቶች በግል ኢንቨስተሮች ይዞታ በመላ ሃገሪቱ ተንሰራፍተዋል፡፡

በሌሎች የልማት ዘርፎችም የተገኙት ውጤቶች የትየሌለ ናቸው፡፡
በመላ አገሪቱ በበጋና በክረምት ወራት የሚኬድባቸው ጥርጊያ መንገዶች ከሰላሳ ሶስት ሺሕ ኪሎ ሜትር ወደ ስድሳ ሺሕ ኪሎ ሜትር ከፍ ብሏል፡፡ ከጥቂት ዓመታት በፊት በአዲስ አበባና በድሬዳዋ ከተሞች ታጥሮ የነበረው የዓለም ዓቀፍ በረራዎችን የሚያስተናግደው የኢንተርናሽናል አውሮፕላን ማረፊያዎች ቁጥር በዛሬይቱ ኢትዮጵያ የአዲስ አበባውን እጅግ ዘመናዊ ማድረግን ጨምሮ በድሬዳዋ፣ በአክሱም፣ በላሊበላ፣ በአሶሳ፣ በባህርዳር፣ በደብረዘይት፣ በጎንደር፣ በጋምቤላ፣ በአሰላ፣ በጅጅጋ፣ በጅማ፣ በመቀሌና በሁመራ ከተሞች የተንጣለሉ ዓለም ዓቀፍ ደረጃዎችን የጠበቁ የግዙፍ አውሮፕላን ማረፍያ ጣብያዎች አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡

በማህበራዊ ዘርፍ የተመዘገበው ውጤት ለአብነት የአንደኛ ደረጃ ት/ቤት ሽፋን በ1993 ዓ.ም ከዘጠኝ ዓመታት በፊት 60% ያህል የነበረው ዘንድሮ በ2002 ዓ.ም ወደ 97% ከፍ ብሏል፡፡ በሃገራችን ሁለት ዩኒቨርስቲዎች የነበሩበት ገፅታ ተቀይሮ 21 የመንግስት ዩኒቨርስቲዎች በራቸውን ወለል አድርገው በመክፈት ወጣቱን የትምህርት ጥማቱን የሚያረካበት ቧንቧ ሆነዋል፡፡ ከሁለት ዓመታት በኋላ ወደ ተግባር የሚሸጋገሩና ግንባታቸው በመፋጠን ላይ የሚገኘው ዓስር ተጨማሪ የመንግስት ዩኒቨርስቲዎች ስራ ላይ ሲውሉ የከፍተኛ ትምህርትን ፍትሃዊ ስርጭት በሁሉም የሃገሪቱ መአዘናት ያሟላሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡ እንግዲህ የትምህርቱን ዘርፍ ስናነሳ መንግስት በጀት በእርከኑ የሚተዳደሩትን ብቻ እንጂ በመላ የሃገሪቱ አከባቢ በሁሉም ደረጃዎች እንደ አሸን የፈሉትን የግል የትምህርት ተቋማት ቤቱና ተጠቃሚው ይቁጠራቸው ብለን እንለፋቸው፡፡ ከዚህ ከማህበራዊ ዘርፍ

ሳንወጣ ሳይጠቀስ የማያልፈው ሃገሪቱ ባለፉት ጥቂት ዓመታት በጤና ዘርፍ ያስመዘገበችው ውጤት አንዱ ነው፡፡

ከዓስር ዓመታት በፊት የኢትዮጵያ ህዝብ አማካይ የእድሜ ዘመን ወይም ደግሞ በህይወት የሚኖርበት ዘመን 47 ዓመት ነበረ፡፡ ዛሬ ይኸው አማካይ ዕድሜ ሃምሳ አምስት ደርሷል፡፡ በ1983 ዓ.ም በመላ ሃገሪቱ የነበረው የሆስፒታሎች ቁጥር ሰባ ሁለት ብቻ ነበሩ፡፡ በአሁኑ ጊዜ ይህ አሃዝ ወደ አንድ መቶ ሰማንያ ከፍ ብሏል፡፡ በጉልህ የምናያቸው የአዲስ አበባን ጉዳይ ስናነሳ 1983 ዓ.ም ከመዲናችን ሁለት የግል ሆስፒታሎች ነበሩ፡፡ ዛሬ ይህ ቁጥር ወደ ሰላሳ ደርሷል፡፡

ከአምስት ዓመታት በፊት ከተካሄደውና የሂደቱ ዴሞክራሲያዊነት በሽብርና በስልጣን ሱሰኝነት በታወሩ ነውጠኞች የአመፅና የጥፋት ድግስ ንፁኃንን ሰለባ አድርጎ ከተደመደመው የ1997 ዓ.ም ብሄራዊ ምርጫ ሁነኛ ትምህርት በመቅሰም በአሁኑ ጊዜ በሰከነ ሁኔታ በመካሄድ ላይ ያለው የምርጫ ሂደት ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሰጥቶ በመቀበል መርህና በግልፅ ውይይት በደረሱበት ስምምነት መሰረት የመንግስት በጀት በጋራ የተመደበላቸው የሚድያ አጠቃቀም ፍትሃዊ ስርዓት ተበጅቶላቸው የጋራ ችግሮችን በመግባባትና በውይይት የሚፈቱባቸው የምክክር መድረኮች አቋቁመው በሰለጠነ መንገድ የምረጡኝ ዘመቻቸውን እያከናወኑ ናቸው፡፡ ባጠቃላይ ኢትዮጵያ እያሳየች ካለችው የፖለቲካ ብስለት በመነጨም ሃገራችን የአፍሪካን አህጉር በልዩ ልዩ መድረኮች ትወክል ዘንድ ከፍተኛ አመኔታና ሃላፊነት ተጥሎባታል፡፡ G-8 እየተባለ የሚታወቀው የበለፀጉት ሃገሮች ስብስብና ከዚያም ትንሽ ሰፋ ባለው የG-20 የበለፀጉት ሃገሮች መድረክ ላይ ተገኝታ የአፍሪካን ጥቅም በማስጠበቅ ሁነኛ ሚና መጫወቱን ቀጥላበታለች፡፡ ከዚህም ሌላ በነዚህ መድረኮች ባሳየችው ፋይዳ ያለው ውጤታማ ተሳትፎ አሁንም አህጉራችንን በመወከል በዓለም የአየር ንብረት የመሪዎች ስብሰባ ላይ እንድትገኝ ሙሉ አመኔታ ተጥሎባት ሃላፊነትዋን በሚያስመካ መልኩ እየተወጣች ትገኛለች፡፡

ይኸንን አሌ ሊባል የማይቻለውን ማንም በዓይኑ በብረቱ አይቶ በተጨባጭ ህልውናውን ማረጋገጥ የሚችለውን ግዙፍ ስታቲስካዊ መረጃ ማቅረባችን ለጉዳዩ ባለቤት ለኢትዮጵያ ህዝብና መንግስት በርቀት ከምንገኝበት ሃገር ላይ ሆነን ለመግለፅ ነው ቢባል ለቀባሪ አረዱት እንደሚሆንብን ከቶ ልንስተው የምንችለው ጉዳይ አይደለም፡፡ ነገሩ ወዲህ ነው፡፡ በአከባቢያችን በእናውቅልሀአለን ግብዝ ፈሊጥ ተወጥረው የዓለምን ህብረተሰብ በተሳሳተና ኢትዮጵያን ዕልመት በሚያላብስ የጥላሸት መቀባት ዘመቻ ላይ እንቅልፍ አጥተው የተሰማሩት ጥቂት ዕንፈኞችና ሃገራዊ ስሜት በራቃቸው አስመሳዮች ሰሞኑን ከዚህም ከዚያም በመጠራራት በቅብብሎሽ የተያያዙትን የቀቢፀ ተስፋ የገደል ማሚቶ ጩኸት ምላሽ እንዲሆን ከልማቱ ውቅያኖስ በጭልፋ ማቀበላችን ነው፡፡

እጅግ የሚገርመው መላ ብሄር ብሄረሰቦቿና ህዝቦቿ በአንድ ድምፅ ሰላማዊ፣ ዴሞክራሲያዊ፣ ፍትሃዊ፣ ነፃና በሁሉም ወገን ተአማኒነትን ያተረፈ ምርጫ ለማካሄድ ባቀነቀኑበት ዋዜማ ላይ ሆነው በሰሚናር ጋጋታ፣ በመግለጫ ቱማታና በአልሞት ባይ ተጋዳይነት የቁራ ኡኡታቸውን የሚያቀልጡበት ጥቂት ሃሳዌ መሲሃን የህዝቡን መስዋእትነትና ጥረት መና ለማስቀረት የመብቱና የጥቅሙ ተሟጋች ነን ብለው ማሸርገድ መቀጠላቸው ነው፡፡ ይባስ ብለውም የትላንቱን የስደትና የረሃብ ቁስሉን በመነካካት ሆደ ባሻነትን ከመቀስቀስ አንስቶ አንቱ የተሰኙ የምርጫ ታዛቢዎች የመፃኢውን ምርጫ ነፃና ዴሞክራሲያዊ ሂደት እንዳይከታተሉ እስከ መወትወትና ደንቃራዎች እስከ መሆን ጨምሮ የአስመሳይ ተቆርቋሪነት ውልድ እስከሆነው የአዞ እንባ አውራጅነት ሙሾ ላይ ተሰማርተዋል፡፡

የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች የሚበጃቸውን ስርዓት መገንባት የጀመሩትና መብታቸውንም በእርግጠኝነት በእሱና በእሱ ዋስትናነት ብቻ እንደሚያረጋግጡት ቅንጣት ታህል አይጠራጠሩም፡፡ጥቂቶች በአፈ ጮሌነትና ብልጣብልጥነት የሚያደርጉት የእናውቅልሃለን እጥፍ ዘርጋም በህዝቡ ኪሳራ ራሳቸውን በአቋራጭ ስልጣን እርካብ ላይ ቁጢጥ በማለት አድሎአዊ ስርዓታቸውን ለመጫን የሚያደርጉት መፍጨርጨር ስለሆነ የህዝብ ወገን የሆነ ሁሉ ይኸንን ጉንጉን ሴራቸውን በማጋለጥና በማክሸፍ የበኩሉን ድርሻ ይወጣ እንላለን፡፡

የትግራይ ተወላጆች ማህበር ፅ/ቤት
ዋሽንግተን ዲሲ

April 6, 2010